# “የአጥር ወፍ አትስማሽ” ሥርዓተ ክዋኔና ፋይዳ በጃቢ ጠህናን ወረዳ

መስፍን ፈቃዴ[1]


## አኅጽሮተ ጥናት

ይህ ጥናት "የአጥር ወፍ አትስማሽ" ሥርዓተ ክዋኔና ፋይዳ በጃቢ ጠህናን ወረዳ በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን፤ ዋና ዓላማው "የአጥር ወፍ አትስማሽ" ሥርዓተ ክዋኔ ማን፣ ምን፣ እንዴት፣ መቼ፣ የት፣ እንደሚከበር እና ያለው ፋይዳ ምን እንደሆነ ማሳየት ነው። ጥናቱ አይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን፤መረጃዎቹ ከካልዓይና ከቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ከዐውዳቸው ተሰብስበው “የአጥር ወፍ አትስማሽ” ስርዓተ ክዋኔና ፋይዳን ከሥርዓተ ክዋኔው ጋር በተያያዘ የሚከወኑ ሀገረሰባዊ እምነቶች እና ብሂላዊ ንግግሮችን ምንነት መርምሯል። የጥናቱ የንሞና ዘዴ ዓላማ ተኮር ሲሆን፤ ከቁልፍና ከተባባሪ መረጃ ሰጪዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ተግባራዊ፣ ተምሳሌታዊ እና ሥነ ልቡናዊ ንድፈ ሀሳቦችን በመጠቀም ተተንትነዋል። በጥናቱ ውጤት መሰረት የአጥር ወፍ አትስማሽ ሥርዓተለ ክዋኔ ሰፊ ጽንሰ ሀሳብን የሚይዝ ሲሆን፤ ከእርግዝና ጀምሮ እስከ ክርስትና ያለውን ጊዜ ሂደት የሚያጠቃልል ነው። አንዲት ነፍሰጡር እናት መውለጃዋ ሲቃረብ፤ ዘመድ ጎረቤቶቿ ምጧ ሳይጠናባት "ከአጥሯ ስር ያለችው ወፍ" እንኳ ሳትሰማ በሰላም እንድትገላገል መልካም ምኞታቸውን የሚገልጹበት ሲሆን፤ ሥርዓተ ክዋኔውን አስመልክቶ ወላዷ በወሊድ ጊዜ የምትመገባቸውን ምግቦች እና ፈሳሾች በጋራ በመሰባሰብ ከማዘጋጀት ጀምሮ እስከ ክርስትና ማስነሳት ድረስ ሊዘልቅ የሚችል ክዋኔያዊ ሥርዓትን የሚያካትት ነው። ሰዎች ነፍሰጡሯን “የአጥር ወፍ አትስማሽ” በማለት መልካም ምኞታቸውን እንደሚገልጹላት ከመረጃ ሰጪዎች ለመገንዘብ ተችሏል። ክዋኔያዊ ሥርዓቱ ለነፍሰጡር እናቶች ካላው ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ሥነ ልቦናዊ ፋይዳ አንጻር ባህላዊ እሴቱን ለወጣቱ ትውልድ የማሳወቅ ሥራ በባህል ቱሪዝም ባለሙያዎች አማካኝነት መሰራት እንደሚገባ ምክረ ሐሳብ በመስጠት ጥናቱ ተጠናቋል።


ቁልፍ ቃላት፡- [የአጠር ወፍ አትስማሽ፣ስርዓተ ክዋኔ፣ጃቢ ጠህናን]

## 1. የጥናቱ ዳራ

ሀገረሰባዊ ልማድ (Social Folk Custom) አንዱ የፎክሎር ዘውግ ነው። ሀገረሰባዊ ልማድ ከአራቱ የፍክሎር የጥናት መስኮች አንዱ እንደሆነ ይገለጻል (Dorsen 1972፡51)፤ (ፈቃደ 1991፡10-15)። “ሰዎች አጥብቀው የያዟቸው እምነቶችና ልማዶች መነሻ ምንጫቸው ምንድን ነው? የተወሰኑ ሥርዓቶችንና እምነቶችንስ ለምን ይከተላሉ? እና የመሳሰሉ ጥያቄዎችን በተለይ ፈላስፎች፣ ደራሲያን፣ ሥነ ሰበኞችና ፎክሎረኞች ጊዜ ወስደው የተመራመሩባቸውና ዛሬም የሚመራመሩባቸው ጥያቄዎች ናቸው” (ፈቃደ 991፡13)። ዘውጉ ማኅበረሰብቡ በተደጋጋሚ የሚከውናቸው ድርጊቶችን ቅደም ተከተላዊ ሥርዓት መሰረት በማድረግ የሚቀርቡ ጥበቦች ጥቅል መጠሪያ ሲሆን፤ በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ከእምነታዊ በዓላት፣ ከሰብል ማምረት፣ ከሕይወት

---

1.PhD in Folklore and Literature: ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ መምህር፣ ማኅበራዊ ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ (አማርኛ) ቋንቋ ትምህርት ክፍል፤ +251911583425፣ email: mesfin_fekadie@dmu.edu.et

ለውጥ ማለትም ከውልደት፣ ከጋብቻ፣ ከእርግዝና፣ ከሞት አሊያም ከኢኮኖሚያዊ እና ከማኅበራዊ ደረጃ ለውጥ ጋር ተያይዘው የሚከበሩ ሥርዓተ ከበራዎችን በሙሉ ያካትታል (Sims and Stephnes 2005፡90-92)[2]።

ሀገረሰባዊ ልማድ ከማኅበረሰብ ጋር በጥብቅ የተሳሰረ የዕለት ከዕለት ክዋኔ ከመሆኑም በላይ በስፋት የሚከወኑ ተግባራትን የያዘ ዘውግ ነው። በሀገረሰባዊ ልማድ ስር የሚመደቡ የፎክሎር ዘርፎች ሀገረሰባዊ እምነት፣ ክብረ በዓላት፣ መዝናኛዎችና ጨዋታዎች፣ ይገኙበታል (ፈቃደ 99፣13፤ Canda 1988፡ 209)። ሀገረሰባዊ ልማድ በአንድ በኩል ማኅበረሰቡ በእምነቱ፣ በፖለቲካው ወይም በሌላ ሥነ ልቦናዊ ምክንያት የሚያከብራቸው እንደ ገና፣ ጥምቀት፣ እሬቻ፣ ፍቼ ጨምበለላ እና የመሳሰሉትን፤ በሌላ በኩል የከዋኙን ማኅበረሰብ የለውጥ ሽግግር ማለትም ጋብቻ፣ ነፍሰጡርነት፣ ውልደት፣ ክርስትና፣ ሞት የመሳሰሉትን መሰረት አድርጎ የሚያከብራቸው በዓላት ሁነት በመባል ይጠራሉ። ይህ ሁነት ፌስቲቫል፣ ክብረ በዓል፣ ሥነ ስርዓት እና ሥርዓተ ከበራን የሚያካትት ሲሆን፤ “ብቃተ ወግ” የስርዓተ ከበራ አንዱ ክፍል ነው (Rappaport 1992 ፡75-78፤ Gennep 1960:1-3)። “ብቃተ ወግ” (Rities of passage) የአንድ ማኅበረሰብ አባል ከነበረው ማኅበራዊ ደረጃ ሲቀይር የሚከወን ሲሆን፤ የለውጡ ምክንያት የእድሜ፣ የኢኮኖሚ ወይም የማኅበራዊ ጉዳይ ሊሆን ይችላል።

ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች ሀገር፤ የብዙ ባህል መገኛ፣የቆየ ታሪክ ባለቤት በመሆኗ በተለያየ አከባቢ በተለያየ ብሔር የተለያዩ የ“ብቃተ ወግ” ሥርዓተ ከበራዎች ይከናዎናሉ። ለምሳሌ የሰርግ፣ የውልደት፣ የክርስትና የሞት ሥርዓት አከባሪዎች እንደብሄሩ ባህል እንደ ግለሰቡ ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ቢለያይም በመሰረታዊ የከበራ ሂደቱ ላይ ተመሳስሎው ጎልቶ ይታያል። ከእነዚህ የ“ብቃተ ወግ”ሥርዓተ ከበራዎች መካከል የነፍሰጡር እናቶች መልካም ምኞት መግለጫ የሆነው “የአጥር ወፍ አትስማሽ” ሥርዓተ ክዋኔ ይገኝበታል።

ሥርዓተ ክዋኔው ነፍሰጡር የሆነች ሴት ልትወልድ በተቃረበችበት ጊዜ በአራስነቷ ወቅት በወሊድ ምክንያት የፈሰሳትን ደም ለመተካት፤ ሰውነቷን ለማጠንከር (ወደ ቀደመ ብቃቷ እንድትመለስ ለማድረግ) እና የወለደችውን/ቻትን ሕጻን በተገቢው መልኩ ማጥባት እንድትችል የሚያስችሏትን የምግብ ዝግጅቶች ከዘመድ ወዳጅ ጎረቤት ጋር በመሆን በጋራ ስራዎች የሚከወኑበት፤በተለይም ነፍሰጡር የሆነችው ሴት ለተለያየ ፍርሃትና ጭንቀት እንዳትጋለጥ በወሊድ ልምድ ያላቸው እናቶች የሕይወት ልምዳቸውን በማጋራት ለነፍሰጡር ሴት ሥነ ልቦናዊ ድጋፍ እና እንክብካቤ ከማድረግ ጀምሮ እስከ ክርስትና ማስነሳት ድረስ ያለውን ጊዜ ሂደት የሚያካትት ሰፊ ጽንስ ሀሳብ ነው።

በአጠቃላይ ነፍሰጡሯ በማንኛውም መልኩ በአራስነቷ ወቅት የሚያስፈልጓትን መሰረታዊ የመታረሻ ግብአቶች በመተጋገዝና በመረዳዳት መንፈስ የሚያሟሉበት አንዱ መንገድ ነው። በመጨረሻም ባህሉን መሰረት አድርጎ አቅም በፈቀደ መጠን ዝግጅቱ ሲጠናቀቅ “የአጥር ወፍ አትስማሽ” በማለት መልካም ምኞታቸውን በመግለጽ የመውለጃ ጊዜዋን ይጠባበቃሉ፤ ከወለደች በኋላ እራሷንና

2. በዚህ ጥናት ውስጥ የሚገኘው የዘመን አቆጣጠር የተገለጸው በአማርኛ የተጻፉ መጻሕፍት በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ሲሆን፤ በእንግሊዝኛ የተጻፉት ግን በጎርጎሮሳዊያን የዘመን አቆጣጠር መሰረት የቀረቡ ናቸው፡፡

ሕጻኑን/ኗን ቤት ያፈራውን በመያዝ የመመገብ ሥርዓት ይካሄዳል፤ ከዚያም ክርስትና አስነስታ ወደ መደበኛው የማኀበራዊ ተሳትፎ እስክትመልስ ድረስ ኢኮኖሚያዊና ሥነ ልቦናዊ ድጋፉ ይቀጥላል። በዚህ መልኩ እርግዝና ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ደረጃዎች ለነፍሰጡሯ የመልካም ምኞት መገለጫ ክዋኔዎች በየጊዜ ሁነቶች ተከፋፍለው ይደረጋሉ። በተለያዩ ተሞክሮዎች (ግላዊና አካዳሚያዊ) ለማስተዋል እንደተሞከረው "ከአጥር ወፍ አትስማሽ" የነፍሰጡር እናቶች የመልካም ምኞት መግለጫ ሥርዓተ ክዋኔ ላይ ትኩረት ሰጥቶ፣ በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ ዘንድ ተወስኖ በስፋትና በጥልቀት የተሰራ ወይም የቀረበ የምርምር ስራ ማግኘት አልተቻለም። ነገር ግን ከጋብቻ ሥርዓት ጋር በተያያዘ የተሰሩ ጥናቶችን ለማየት ተሞክሯል። የ(ሥራዬ 2005)፣ የ(አፀደ 2007 ዓ.ም.)፣ የ(ሽታዬ 2011 ዓ.ም.)፣ የ(ሙሉቀን 2011ዓ.ም.)፣ የ(ሉባባ 2012 ዓ.ም.)፣ የ(መሐመድ 2012 ዓ.ም.) እና የ(እንድሪስ 2012 ዓ.ም.) የምርምር ስራዎች ተቃኝተዋል።

የቀረቡት ጥናቶች በዋናነት ትኩረታቸው ከሥርዓተ ጋብቻ ጋር በተያያዘ የሚደረጉ ሥርዓተ ክዋኔዎችን የሚዳስሱ ናቸው፤ ይሁን እንጅ ይህ ጥናት ይዞት ከተነሳው ርዕሰ ጉዳይ አንጻር ዳሰሳ ከተካሄደባቸው ምርምሮች በአይነቱ የተለየ ነው። ጥናቱ በርዕሰ ጉዳይ መልኩ ራሱን ችሎ መጠናቱ የባህሉ ባለቤቶች በቃላዊ ተስተላልፎ እየከወኑት ያለውን ሥርዓት ለይቶ፣አደራጅቶና ሰንዶ በማስቀመጥ አንድም ለተተኪው ትውልድ ክዋኔያዊ ስርዓቱን እንዲሻገር ለማድግ፤ በሌላ መልኩም ክዋኔያዊ ሥርዓቱን ምን እንደሚመስል በማስተዋወቅ ነፍሰጡር እናቶች ከእርግዝና ጋር በተያያዘ ከሚከሰትባቸው የኢኮኖሚ፣ የማኀበራዊ እና የሥነ ልቦና ጫናዎች እንዲወጡ ከማድረግ አንጻር ያለው ፋይዳ የጎላ ነው። በአካዳሚው ዘርፍም ያለውን እውቀት ከመሰነድ፣ ከመተንተንና ከማስተዋወቅ ባለፈ በዘርፉ ላይ ተጨማሪ ምርምሮች እንዲካሄዱበት ለማድረግ ያገለግላል።

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በጃቢ ጠህናን ወረዳ ውስጥ "የአጥር ወፍ አትስማሽ" ሥርዓተ ክዋኔና ፋይዳን መተንተን ሲሆን፣ ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት። ለነፍሰጡር እናቶች የሚካሄደውን ሥርዓተ ክዋኔ ማሳየት፣ የሥርዓተ ክዋኔውን ማኅበረ ባህላዊ ዳራ መግለጽ፣ ከሥርዓተ ክዋኔው ጋር የሚፈጸሙ ሀገረሰባዊ እምነቶችን ማብራራትና ከክዋኔው ጋር በተያያዘ የሚነገሩ ብሂላዊ ንግግሮችን ይዘት መተንተን የሚሉት ይገኙበታል። ጥናቱ "የአጥር ወፍ አትስማሽ" ሥርዓተ ክዋኔን ምንነት ከማሳየቱም በላይ ከክዋኔው ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ ሀገረሰባዊ እምነቶችን ሰንዶ ለመያዝ ያስችላል ተብሎ ይታሰባል። ጥናቱ ከይዘት እና ከቦታ አንጻር ተወስኖ የቀረበ ነው። የጥናቱ ወሰን ከቦታ አንጻር በምዕራብ ጎጃም ዞን በጃቢ ጠህናን ወረዳ ውስጥ ካሉ ሰላሳ ዘጠኝ ቀበሌዎች መካከል በአራቱ ማለትም፡- አርባዋሽ፣ ዘንገባል፣ አዘመር የባዲ እና ፈተገም ድግት ቀበሌዎችን ተተኳሪ ናሙና አድርጎ ተጠንቷል። እነዚህ ቀበሌዎች በጥናቱ እንዲካተቱ የተደረገበት ምክንያት ከከተማ የራቁ በመሆናቸው ክዋኔያዊ ስርዓቱ ዛሬም ድረስ የሚካሄድ ስለሆነ በአንጻራዊነት ባህላዊ እሴቱ ዘመናዊነት ካመጣው የአስተሳሰብ ተጽእኖ ስር ያልወደቁ በመሆናቸው የማኀበረሰቡን እሴት ያሳያሉ በሚል እሳቤ የተመረጡ ናቸው። ጥናቱ ከይዘት አንጻር ነፍሰጡር እናቶች ከእርግዝናቸው ጀምሮ ወልደው ክርስትና እስከሚያስነሱ ድረስ ባላው የጊዜ ሂደት ላይ ያተኩራል። ምክንያቱም ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ወሊድ እና ድህረ ወሊድ የተሳሰሩ ባህላዊ የሽግግር ጊዜ በመሆናቸው ነው።


“የአጥር ወፍ አትስማሽ” ሥርዓተ ክዋኔ የአከባበር ሥርዓቱ ይለያይ እንጂ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ቤቢሻወር በመባል እንደሚከበር መረጃዎች ይጠቁማሉ (Gladys 2019፡78-80)፤ (Turner 1969፡ 95-96)። በኢትዮጵያም “የአጥር ወፍ አትስማሽ” በመባል ለረጅም ጊዚያት ሲከበር እንደቆየ ጥናቶችና መረጃ ሰጪዎች ይጠቁማሉ (ሙሉቀን 2011፡44)። በኢትዮጵያ በእስልምና እምነት ተከታዩች ዘንድ “ፋጢማ ቆሪማ” በመባል እንደሚከበር ይገለጻል (ሙሐመድ 2012፡57)። በጥናቱ ተተኳሪ አካባቢ የሚገኙ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ የማኅበረሰብ ክፍሎች “የአጥር ወፍ አትስማሽ” ሥርዓተ ክዋኔን መቼ እንደሚያከብሩ፣ በምን መልኩ ሥርዓተ ክዋኔውን እንደሚከውኑ እና በክዋኔ ሥርዓቱ ላይ የሚከዎኑ ሀገረሰባዊ እምነቶች ፋይዳቸው ምን እንደሚመስል በመረጃ ላይ ተመስርቶ ትንተና ቀርቧል።

## 2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ጥናቱ እንዲካሄድ መነሻ የሆነው ሀሳብ በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ የሚገኙ በእድሜ ገፋ ያሉ እናቶች በአመዛኙ ያለ ሐኪም እርዳታ ያለምንም ኮሽታ በርከት ያሉ ልጆችን ተገላገልው፣ያን ጊዜ በጋራ በመተጋገዝ ችግርና ጭንቀትን ለማቃለል የምናደርጋቸው የትብብር ስራዎች እንዲሁም ልጆችን ወልዶ በማሳደግ የተሻለ ልምድ ያላቸው እናቶች ያሳለፉቸውን ክፉ ደግ የሕይወት ተሞክሮዎች እያሰቡ ልምዳቸውን የሚያጋሩበት ሁነት አሁን አሁን እንደ ዋዛ እየቀረ በመምጣት ላይ ይገኛል። ነገር ግን እነዚያ የመተባበሪያና የመተጋገዥያ ሥርዓቶች ነፍሰጡር እናቶችን ያጠነክሩን ነበር፤የሞራል ስንቃችንም ነበሩ፤ሲሉ መስማቱና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየታየ ባለው የባህል ለውጥ እና የዘመናዊ አስተሳሰብ ምክንያት ከዚህ በፊት ይከወኑ የነበሩ የቅድመ ወሊድ፣ የወሊድ እና የድህረ ወሊድ ጊዜ ሥርዓተ ክዋኔዎች እየቀሩ በዘመናዊ ቤቢ ሻውር እየተተኩ በመምጣታቸው የክዋኔውን ምንነት፣ፋይዳ እና ቀጣይነት በጥናት ላይ ተመስርቶ በመግለጽ ማኅበራዊ እሴቱን ማስተዋወቅና ሥርዓቱ እንዲቀጥል ያለ ፍላጎት ለጥናቱ መነሻ ሀሳብ ሆኗል።

## 3. የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ

የጃቢ ጠህናን ወረዳ በ1933 ዓ.ም. እንደተመሰረተ መረጃዎች ያሳያሉ (በ2015ዓ.ም. ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት እና ከመስክ ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ከተገኘ መረጃ የተጠናቀረ)። ጃቢ ጠህናን በምዕራብ ጎጃም አስተዳደር ዞን ስር ከሚገኙ ዘጠኝ ወረዳዎች መካከል አንዱ ሲሆን፣ ወረዳውን በስተ ሰሜን ሰከላና ቋሪት፣ በስተደቡብ ደምበጫ፣ በስተ ምስራቅ ደጋዳሞት እና በስተ ምዕራብ ደግሞ ቡሬ ወረዳዎች ያዋስኑታል። ወረዳው የአማራ ክልል ከተማ ከሆነችው ባህር ዳር በስተ ምዕራብ 180 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን ከአዲስ አበባ በስተ ሰሜን አቅጣጫ 350 ኪ.ሜ ርቅት ላይ ይገኛል።




ፎቶ፣ ፡- የኢትዮጵያን፣ የአማራን፣ የምዕ/ጎጃምን እና የጃቢ ጠህናንን ወረዳ የሚያሳይ ካርታ
ምንጭ፡- የክልል፣ የዞን እና የወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ጽ/ቤት

የጃቢ ጠህናን ወረዳ 39 የገጠርና 2 የከተማ ቀበሌዎች ያሉት ሲሆን ከተማ እና ገጠር ዙሪያ አስተዳደር ተብሎ የተከፈለ ነው። ፍኖተሰላም የምዕራብ ጎጃም ዞን እና የጃቢጠህናን ወረዳ ዋና ከተማ በመሆን በማገልገል ላይ ይገኛል (በ2015ዓ.ም. ከወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ጽ/ቤት ከተገኘ መረጃ የተጠናቀረ)።

## 4. የጥናቱ ሥነ ዘዴ

በዚህ ክፍል የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የናሙና አመራረጥ እና የመረጃ መተንተኛ ስልቶች ምን እንደሚመስሉ በዝርዝር ቀርቧል።

### 4.1. የጥናቱ አይነት

ይህ ጥናት በሰዎች አመለካከት፣ አስተሳሰብና ባህሪ ላይ የሚያተኩር፣ በገለጻና በትንተና ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ዓይነታዊ ነው። አይነታዊ የምርምር ዘዴ ከቁጥር ይልቅ በገለጻና ትንተና ላይ ሰፊ ሀሳብን ለማቅረብ ዕድል ይሰጣል (ያለው 2004፡35)። ጥናቱ “የአጥር ወፍ አትስማሽ” ሥርዓተ ክዋኔንን በቅደም ተከተል በገለጻና ትንተና የሚያቀርብ በመሆኑ አይነታዊ የምርምር ዘዴን ይከተላል፤ አንዲት ነፍሰጡር እናት እርግዝናዋን እራሷና ቤተሰቦቿ ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ ከሚደረጉ እንክብካቤዎችና ክትትሎች ጀምሮ ክርስትና እስክታስነሳ ድረስ የሚደረጉ ዋና ዋና ክዋኔዎችን፣ ሀገረሰባዊ እምነቶችን እና አባባሎችን ከዐውዳቸው በመሰብሰብ ተግባራዊ፣ተምሳሌታዊ እና ሥነ ልቡናዊ ንድፈ ሀሳቦችን በመጠቀም ትንተና ተካሂዷል። ተምሳሌታዊ ንድፈ ሀሳብን በመጠቀም የባህሉ ባለቤቶች ለዘመናት ሥርዓተ ክዋኔውን በማስቀጠል ዛሬም ድረስ እየፈጸሙት የሚገኙበትን ፋይዳ ለማሳየት፣ ተምሳሌታዊ ንድፈ ሀሳብን በክዋኔያዊ ሥርዓቱ ላይ የሚደረጉ ትዕምርቶችን ውክልና ከባህሉ አንጻር ያላቸውን ፍች ለመተንተን እንዲሁም ሥነ ልቦናዊ ንድፈ ሀሳብን በነፍሰጡር እናቶች ላይ ከእርግዝና ጋር በተያያዘ የሚከሰተውን የሥነ ልቦና ጫናና ጭንቀት ምን እንደሚመስል ለማሳየት ጥቅም ላይ ውለዋል።

### 4.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

መረጃዎች ከቀዳማይና ከካልአይ ምንጮች ተሰብስበዋል። ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ምልከታ፣ቃለ መጠይቅ እና የቡድን ውይይት ዘዴዎች ናቸው። በምልከታ ከተሰበሰቡ መረጃዎች መካከል ነፍሰጡር እናቶች "በአጥር ወፍ አትስማሽ" ሥርዓተ ክዋኔ አማካኝነት መውለጃቸው እየተቃረበ ሲመጣ በወሊድ ጊዜ የሚመገቧቸው የምግብ ዝግጅቶች ምን እንደሚመስሉ በቼክሊስት አማካኝነት አስር ኢ-ተሳትፏዊ ምልከታ ለማካሄድ ተችሏል። በጥናቱ ተተኳሪ አካባቢ ካሉ እድሜያቸው የገፉ አስር እንዲሁም ከወጣት አስር በድምሩ ሃያ ሴቶች በዓላማ ተኮር የናሞና ዘዴ ተመርጠው ነፍሰጡር እናቶች የመውለጃ ጊዜያቸው ሲቃረብ በወሊድ ጊዜ የሚመገቧቸው የምግብ ዝግጅትን በተመለከተ በቃለ መጠይቅ መረጃዎች እንዲሰበሰቡ ተደርጓል። በምልከታና ቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ትክክለኛ እና አስተማማኝ እንዲሆን እድሜን እና ማኅበራዊ ደረጃን እንዲሁም በትምህርትም ሆነ በእድሜ ባለጠግነት ታሪኩን እና ባህሉን የሚያውቁ ሰዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በአካባቢው ነዋሪ የሆኑ ሽማግሌዎች፣ ወጣቶች እና የሃይማኖት አባቶች የተካተቱበት የቡድን ውይይት ተካሂዷል። ለቡድን ውይይቱም የተመረጡ ሰዎች ሁለት ሽማግሌዎች፤ ሶስቱ ወጣቶች፤ ሁለት የሃይማኖት አባቶች በድምሩ ሰባት መረጃ ሰጪዎች ናቸው። ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ደግሞ ቤተ መጻሕፍትን፣ ድረገጾችን፣ መጣጥፎችን በመጠቀም ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጽንሰ ሀሳቦችና ንድፈ ሀሳቦች የተሰበሰቡበት ነው፡

### 4.3 የናሙና አመራረጥ እና የመረጃ መተንተኛ ስልት

ጥናቱን ለማካሄድ ከርዕሰ ጉዳይ፣ ከገንዘብ እና ከጊዜ አንጻር ሁሉንም ማካተት ስለማይቻል ከአጠቃላይ ተጠኝ ወረዳ ውስጥ ማኅበረሰቡን ሊወክሉ የሚችሉ ቀበሌዎችና መረጃ ሰጪዎች በዓላማ ተኮር እና በጠቋሚ የናሙና አመራረጥ ዘዴ እንዲመረጡ ተደርጓል።

በምልከታ፣በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን በፈርጅ በፈርጁ በመለየት፣በማደራጀትና በአይነታቸው በመከፋፈል በገላጭ የትንተና ዘዴ ተተንትነው ቀርበዋል።፡

## 5. የጥናቱ መረጃ ትንተና

በዚህ ክፍል "የአጥር ወፍ አትስማሽ" ሥርዓተ ክዋኔና ፋይዳ ምን እንደሚመስል የመረጃ ትንተና የተደረገበት ነው።

### 5.1 "የአጥር ወፍ አትስማሽ" ምንነት

"የአጥር ወፍ አትስማሽ"[3] አንዲት ነፍሰጡር ሴት እርግዝና ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ ክርስትና እስከ ማስነሳት ድረስ ያለውን ጊዜ ሂደት የሚያከትት ሲሆን፤ ሂደቱ በተለያዩ ሁነቶች የሚከዎን ሥርዓት

3. የአጥር ወፍ አትስማሽ በውጪው ዓለማ ቤቢሻውር የሚባል ሲሆን ሥርዓተ ከበራውን ና ዓለማውን በተመለከተ እንዲህ ይገለጻል፤ A baby shower is a kind of gift-giving ceremony and party where friends and family of the expectant mother and/or couple come together to celebrate the expected birth of a baby, along with the woman's journey into motherhood. There are many advantages to holding a baby shower, the main one being helping the expectant mother

ነው። ነፍሰጡሯ የመውለጃዋ ሰዓት ሲቃረብ በወሊድ ጊዜ የምትመገበውን የምግብ አይነት ዘመድ ወዳጅ ጎረቤት በመሰባሰብ የገንፎ እና የአጥሚት እህሎችን የሚያዘጋጁበት ሥርዓት አንዱ መገለጫ ነው። በጥቅሉ ነፍሰጡሯ ከወሊድ እስከ ክርስትና ማስነሳት ባለው ጊዜ የሚያስፈልጋትን ነገር ቀድማ እንድታዘጋጅ የሚረዳት ሲሆን፤ያልተከናወኑ የተለያዩ ተግባራት እንዲከናዎኑ ማድረጊያ ሥርዓት መሆኑን መረጃ ሰጪዎች እንዲህ ይገልጻሉ።

> የአጥር ወፍ አትስማሽ" ማለት አንዲት ነፍሰጡር ሴት ምጧ ሳይጠና፣ ጩኸት ሳታሰማ፣ በሰላም፣ በጤና እንድትገላገል የመልካም ምኞት መግለጫ ሥርዓት ማለት ሲሆን፤ በዚህ የክዋኔ ሂደት ወዳጅ፣ዘመድ ጎረቤት ይጠራና ነፍሰጡሯ ከወሊድ ጊዜ ጀምሮ ክርስትና እስከ ማስነሳት ድረስ ባለው ጊዜ ሂደት የምትመገባቸውን የገንፎና የአጥሚት እህሎች የመልቀም፣ የማንፈስ፣ የመፈተግ፣ የመቁላት እና የመሳሰሉ ተግባራት በጋራ የሚከውኑበት ዐውድ ነው። ወላዷ በወሊድ ጊዜ የምትመገባቸውን የእህል አይነቶች እሷ እንኳ እጅ ቢያጥራት ዘመድ ወዳጅ ጎረቤት ከየቤታቸው አሟልተው በማቅረብ ነፍሰጡሯ ለሌሎች ነፍሰጡሮች ከሚደረገው ባህላዊ ዝግጅት ባልተናነሰ መልኩ የሚደረግን የዝግጅት ሂደት የሚገልጽ መሆኑ ይጠቀሳል (የቡድን ውይይት ተሳታፊ 05፤ 06/09/2015 ዓ.ም.)።

በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ ስለ አጥር ወፍ አትስማሽ ያለው ትርጓሜያዊ ይዘት በጣም ሰፋ ያለ ነው። ይህን በተመለከተ በቃለ መጠይቅ የተጠየቁት የጥናቱ ተሳታፊዎች እንደሚከተለው ያብራሩታል።

> የአጥር ወፍ አትስማሽ" አንዲት ሴት ነፍሰጡር መሆኗ ከታወቀ ጀምሮ የምትመረቀው ምርቃት ነው። ዘመድ ሰላምታ ከተለዋወጠ በኋላ ሲሰናበት "የአጥር ወፍ አትስማሽ" ወይም "በቸር ይመልሰን"፤ በማለት የነፍሰጡርነት ጊዜዋን በሰላም ፈጽማ እንዲገናኙ በመመኘት ይሰናበታል። በሌላ በኩል ደግሞ ነፍሰ ጡሯ ድግስ አውጥታ በቤት ውስጥ ገብቶ በልቶ ጠጥቶ የወጣ ዘመድ ጎረቤት በሙሉ የምርቃ ማደማደሚያው "የአጥር ወፍ አትስማሽ" የሚለው አባባል ነው። በሌላ በኩል ነፍሰጡር ወልዳ ስትተኛ ቤተሰቦች የሚመገቡት፤ እሷም የምትታረስበት የጠላ፣ የበርበሬና፣ የሽሮ እና የገንፎ እህል (ሥልቅ) ዝግጅት ላይ የተሳተፉ ሴቶች የዝግጅት ስራውን አጠናቀው ሲጨርሱ "የአጥር ወፍ አትስማሽ" ብለው መርቀው ይወጣሉ። ስለዚህ አባባሉ የአንድ ቀን ሳይሆን ነፍሰጡሯ ማርገዟ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ ወልዳ ማተብ እስከ ማሳሰር[4] ድረስ ያለውን ጊዜ የሚያካትት መሆኑ ይገለጻል ተሳታፊ 17፤ ቃ.ም. 14/05/2015 ዓ/ም )።

---

and/or couple with the expenses. As the women in ancient Roman and Egyptian times did, people now gift mothers-to-be gifts that will help prepare them for caring for their baby. Baby showers are also a great way for expectant mothers to collect advice from her family and friends and for the latter to offer the mother-to-be emotional support. https://www.babydoppler.com

4. ማተብ (ማዕተብ) አንደኛው ፍቺ ምልክት ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ቡራኬ ማለት ነው፡፡ ሥርወ ግሡም “አተበ” አመለከተ፣ባረከ የሚለው የግዕዝ ቃል ነው፡፡ ማተብ ማሳሰር ማለት ሕጻኑን/ኗን እናት አባት የሚከተሉትን እምነት

ከቀረቡት ገለጻዎች መረዳት እንደሚቻለው "የአጥር ወፍ አትስማሽ" ሥርዓተ ክዋኔ የአንድ ቀን መጠሪያ ሳይሆን ዘመድ ወዳጅ ነፍሰጡሯ በሰላም ተገላግላ ደህንነቷ ተጠብቆ ከማኅበረሰቡ ጋር የተለመደ ማኅበረ ባህላዊ እንቅስቃሴዋን እስከትጀምር ድረስ ያለውን የጊዜ ሂደት የሚያካትት መሆኑን ነው። ከእርግዝና እስከ የሕጻን ማተብ ማሳሰር ድረስ ባለው የጊዜ ሂደት በሰላም እንድታልፍ የሚደረግ የመልካም ምኞት መግለጫ ነው። በአጭሩ “የአጥር ወፍ አትስማሽ” ማለት እንኳንስ ጐረቤት ዘመድ ወዳጅ ቀርቶ በጣም ቅርብ የሆነችዋ በአጥርሽ ጥግ ያለች ወፍ እንኳን ሳትሰማሽ ምጥሽ ሳይጸና ግርግር ሳይፈጠር፣ ጫጫታ ሳይኖር በሰላም በጤና ተገላገይ ማለት ነው። ይህ አባባል ነፍሰጡሯ ከሞት አፋፍ ላይ እንዳለች አድርጐ ከመቁጠር እና ከመጨነቅ አሊያም ለእሷና ለሕጻኑ/ኗ ደህንነት ከመጓጓት የተነሳ ያንን የጭንቅ ቀን በሰላም እንድታልፍ የመልካም ምኞት መግለጫ ተደርጎ ይወሰዳል። ምልጃው ነፍሰ ጡሯ ከወለደች በኋላ "ማርያም በሽልም ታውጣሽ[5]/አልጋ ስበሪ" በሚል ሌላ ምልጃ ወይም መማጸን ይተካል። እንዲሁም የሕጻኑን/**ኗን** ለሀጭ ጥገቡ በሚል ብሂል ለአራሷ ልዩ እንክብካቤ ይደረግላታል። የእንክብካቤው ሁኔታ ቅድመ ወሊድ፤ ጊዜ ወሊድ እና ድህረ ወሊድ ክዋኔ በሚል የተከፋፈለ ነው። በእያንዳንዱ ሂደት የሚደረጉ ሀገረሰባዊ እምነቶች እና ክዋኔዎች ምን እንደሚመስሉ እንመልከት።

### 5.2 የቅደመ ወሊድ ስርዓተ ክዋኔ

አንድ ነፍሰጡር ሴት እርግዝናዋ ከታወቀ ጊዜ ጀምሮ በአመጋገብ ሂደት፣ይህንን አትብይ፣ ከዚህ ላይ ተቀማጭ፣ ከዚህ ላይ ተኚ፣ ይህን ልበሽ፣ ይህንን አትልበሽ፣ የሚሉ ምክሮች ከእናት፣ ከአማት፣ ከትልቅ እህት እና ከዘመድ አዝማድ ይለገሳል። እንዲህ የሚደረገው ለእሷና ለአረገዘችው ሕጻን መልካም ምኞትን በማሰብ ነው። በጥናቱ ተተኳሪ ባህል መሰረት ነፍሰጡርነት በእናቶች ላይ የሞት ስጋት ተደርጎ ይወሰዳል። ነፍሰጡር ሴት ራሷን በአለባበስ አጋልጣ እርግዝናው እንዲታወቅ አታደርግም፤ይህን ለመደበቅ ሰፋፊ አልባሳትን ትለብሳለች። በነጠላ ሆዷን ትሸፍናለች። እርግዝናን የመደበቅ ጉዳይ በእሷ ብቻ ሳይሆን በእናት፣ በአማት፣ በእህት፣በባል ላይም ይታያል። ሁሉም ሰው ቢሆን ደፍሮ ነፍሰጡርነሽ አይልም፤ በተለመደው የአከባቢ መግባቢያ ቋንቋ አማካኝነት ይጠራታል። ማለትም፡- “ዝንብ ውጣለች” ወይም “ጉልበቷ ደከሟል” ይሏታል። ይህ ሁሉ መሸፋፈን ከነፍሰጡርነት ጋር ተያይዞ የሚመጣውን የሀሳብ ወይም የጭንቀት መንፈስ ለማለፍ በማሰብ ነው። በማኅበረሰቡ ተለመዷዊ አጠራር ነፍሰጡሯን ነፍሰጡርነትሽን አውቄአለሁ፤ መልካም ነገር እመኝልሻለው ለማለት “በቸር ይመልሰን”፣ “የአጥር ወፍ አትስማሽ”፣“ማርያም ትቅረብሽ” እየተባለች ትመረቃለች፤የመልካም ምኞት መገለጫ የሆኑ አባባሎች ይቀርቡላታል። በቅድመ ወሊድ ጊዜ የመውለጃ ጊዜ ሲቀርብ እናት ወይም ሴት አማት ከነፍሰ ጡሯ ቤት በመምጣት

---

ወደ ተወለደው/ችው ሕጻን የሚያሸጋግሩበት የክርስትና ማስነሳት ሥርዓት መሆኑ ይጠቀሳል (የኢትጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት www.ethiopianorthodox.org.)፡፡

5. በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ አንዷት ሴት ስትወልድ ዘመድ አዝማድ ወዳጇቿ እንኳን “ማርያም ማረችሽ” ብለው ወደቤቱ ይዘልቃሉ፤ ሲወጡ ደግሞ “ማርያም በሽልም ታውጣሽ”፤ “አልጋ ስበሪ ”ብለው የደከመ ሰውነቷ ብርታት እንዲሆናት በስሟ ይደግፏታል፡፡ የአባባሉ ሚስጢር በሰላም፣ በደስታ፣ በፍቅር፣ ወፍረሽና አምሮብሽ የአራስነት ጊዜሽን ጨርሰሽ እንድንገናኝ እንመኛለን ለዚህም ቅድስት ድንግል ማርያም ከአጠገብሽ አትለይሽ ማለት መሆኑን መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ (ተሳታፊ 16፤ ቃ.ም. 06/08/2015 ዓ.ም.)፡፡

ምክር ይለገሷታል። የስራ ጫና እንዳታበዛ ይደረጋል፤ቤተሰብም የተገለጸውን አይነትና ተመሳሳይ ተግባራትን በማድረግ እገዛ እንደሚያደርጉላት መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ (ተሳታፊ 16፤ ቃ.መ. 06/08/2015 ዓ.ም.)።

በቅደም ወሊድ ጊዜ የነፍሰጡሯ ሁኔታ የመረበሽ ስሜት ሳይኖራት የተሸለ ደረጃ ላይ እንድትደርስ (በሥነ ልቦናዋ) የተረጋጋች ከማድረግ አንጻር በቃላት ላይ የተመሰረተ የመልካም ምኞት መገለጫዎችን ከማቅረብ ባለፈ በተግባር የተለያዩ የክዋኔ ሥርዓቶች ይካሄዳሉ፤ ይህንንም በተመለከተ መረጃ ሰጪዎች ሀሳባቸውን በሚከተለው መልኩ ይገልጻሉ።

> በቅድመ ወሊድ ጊዜ ቅቤ ይገዛል፤ ይነጠራል፤ በርበሬ እና ሽሮ ይዘጋጃል። ጠላ ይደረጋል፡ ለቤተሰቡ የሚሆነው የቀለብ እህለ ይፈጫል። ይህ የሚሆነው በሴቶች ሲሆን እናት፣ አማት፣ ጐረቤት እና ጓደኛ በዝግጅቱ ላይ ይሳተፋሉ። በሌለ በኩል ባል ደግሞ አራሷ ልትተኛበት የምትችል ሽንት በቀላሉ አንቆርቁሮ የሚያሳልፍ ሰሌን፣አጉዛ ወይም ዳውጃ ያዘጋጃል። የሕጻን ልብስ እንደ ባህሉ ይሰፋል፤ ሌላው ማኅበረሰብም ቢሆን ነፍሰጡር የሆነች ሴት መንከባከብ የተለመደ ተግባር ነው። ለምሳሌ በመንገድ ላይ ሲያገኟት ቅድሚያ ይሰጣታል፤ የተሸከመችው ነገር ቢኖር ሸክሙን በመቀበል ያሳርፏታል። የተሻለ በሚባል ቦታ እንድትቀመጥ ይደረጋል። ነፍሰጡር ይህ አማረኝ፤ይህ ሸተተኝ፤ማለቷ የተለመደ ነው። በባህሉ መሰረት ነፍሰጡር አማረኝ ያለችውን አቅም በፈቀደ መጠን ማሟላት ግዴታ ሲሆን፤ ይህን አለማድረግ ነውር[6] ተደርጎ ይወሰዳል። (ተሳታፊ 10፣ቃ.መ፣02/06/2015 ዓ.ም.)

በዚህ ቅድመ ወሊድ ጊዜ የተለያዩ ሃይማኖታዊና ሀገረሰባዊ እምነቶች ጋር ተያይዘው የሚከለከሉና የሚፈቀዱ ተግባራት መኖራቸውን በቡድን ውይይት ወቅት ከተነሱ ሀሳቦች እንደሚከተለው መረዳት ይቻላል።

> ነፍሰጡር የሆነች ሴት መጸነሷ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ ፀበል አትጠጣም፤ አትጠመቅም፤ምክንያቱም ጸበሉ ጽንሱን ያስወርዳታል ተብሎ በማኅበረሰቡ ውስጥ ስለሚታመን ነው። መልከ ጥፉ ሰው አታይም፤ ቆንጆ የሆነ ሰው ትራመዳለች፤ምክንያቱም የሚወለደው ሕጻን መልክ የምታየውን እና የምትራመደውን ሰው ይመስላል ተብሎ ስለሚታመን ነው። እንዲሁም ጽንሱን በጣም ያፋፋዋል ተብለው የሚታሰቡ የምግብ አይነቶች ለምሳሌ፡- ድንች፤ ዱባ፣ጥሬ ስጋ፣ጉበት እና የመሳሰሉትን ምግቦች እንዳትበላ ትከለከላለች። ምች እንዳይመታት በሚል በእድር፣ በሰርግ እና በመሳሰሉት ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ በሚደረጉ ስራዎች በመገኘት ወጥ መስራትና ወደ ሚፈለገው ቦታ ተሸክሞ መንቀሳቀስ፤ቅቤ ማንጠር የሚፈቀድ ተግባር

6. ነውር "ህጸጽ፣ ገመና" በማለት ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ይፈቱታል (1948፡634)፤ የኢትዮጵያ መጻሕፍ ቅዱስ ማኅበር መዝገበ ቃላት ደግሞ ነውር የሚለውን ቃል "ውርደት" በማለት ይፈታዋል(1992፡27)፡፡ በዚህ መዝገበ ቃላት ፍቺ መሰረት ነውር ጥሰት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ውርደት ማኅነረሰቡ ከሚከተለው ባህል ውጪ የሆኑ ሰዎች መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በሰዎች ፊት ተቀባይነት አለማግኘትንም ያሳያል፡፡ በአጭሩ ከቀረቡት የመዝገበ ቃላት ፍቺ መረዳት የሚቻለው ነውር የሰውልጅ በሚኖርበት ማኅበረሰብ የሚከተሉትን ማኅበረ ባህላዊ እሴቶች አልቀበልም በማለት በማፈንገጥ ለሚመጣ ችግር ተጠቂ መሆንን የሚያመለክት ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡

አይደለም። ነገር ግን ቀለል ያሉ ሥራዎችን እንድትሰራ እንቅስቀሴ እንድታደርግ ይመከራል፤ ይህም ነፍሰ ጡሯ የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስ ምጡ እንዲቀል ያደርጋል ተብሎ ይታመናል (ተሳታፊ 18፣የቡድን ውይይት፣ 21/09/2015 ዓ.ም.)።

### 5.3 የወሊድ ጊዜ ስርዓተ ክዋኔ

ይህ ወቅት ከምንም በላይ ቤተሰብና የቅርብ ወዳጅ ዘመድ የበለጠ ትኩረት ሰጥቶ ነፍሰጡሯን የሚደግፍበት ሰዓት ነው። ምክንያቱም ዘጠኝ ወር ያረገዘች ነፍሰጡር ምጥ የምትጀምርበትና ዘጠኝ ወር በሀሳብና በእንክብካቤ አብሮ የቆየ ዘመድ ወዳጅ መጨረሻውን ለማየት የሚጓጓበት ወቅት በመሆኑ ነው። ምጡ ቀላል ከሆነ እና ቶሎ ከተገላገለች የሚደረጉ ሥርዓተ ክዋኔዎች ይህን ላደረገ አምላክ በማመስገን ከደስታና እልልታ ጋር ተያይዘው የሚከዎኑ ድርጊቶች በስፋት ይታያሉ፤ ነገር ግን ምጡ ከጠነከረና ነፍሰጡሯ ደም ከመታት (ደም ከፈሰሳት ለማለት ነው) የተለያዩ ሃይማኖታዊ እና ሀገረሰባዊ እምነቶችን ሥርዓተ ክዋኔ በማካሄድ የነፍሰጡሯን ሕይወት ለማትረፍ ጥረት እንደሚደረግ ሁኔታውን አስመልክቶ መረጃ ሰጪዎች እንዲህ ይገልጹታል።

> ትልልቅ እናቶች ትኩስ ጉልቻ[7] በመያዝ ቅድስት ማርያምን ይማጸናሉ። ይህም ቅድስት ማርያም ልጅ ስለወለደች የምጥን ነገር ታውቃለች ተብሎ ስለሚታመን እና የጭንቅ አማላጅ ናት ተብሎ ስለሚታሰብ ነው። ምጥ ሲጠነክር ወንዶች ቀበቶአቸውን፤ ሴቶች መቀነታቸውን ይፈታሉ፤በባህሉ መሰረት መቀነትና ቀበቶ መፍታት ምጥ ያላላል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው። ምጡ ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ ከአንድ ሰው ገድ (መልካም እድል የማግኘት ተስፋ) የሌላ ሰው ገድ ይሻላል ተብሎ ስለሚታሰብ ቡና የሚያፈሉ ሴቶች እየተቀያየሩ ነው። ቡናው ሳይቋረጥ የሚፈላው ከእናት አባት ውቃቤ ያስታርቃል ተብሎ ሰለሚታመን ነው። ወላዷን ከጉኗ ሆኖ ለማጽናናት ወንዶች ደረቷን እና ትከሻዋን ሴቶች መቀመጫዋን ደገፍ አድርገው ይይዛሉ። ጫቅማ ቅጠል ተነጥፎ በኩበት ላይ እንድትቀመጥ ይደረጋል (መቀመጫዋ ላይ ችግር እንዳይፈጠር) በማሰብ ነው። "ጫቅማ" የተባለ ቅጠል ምጥን ያፋጥናል ተብሎ ይታመናል። ካህናት ድርሳነ ሩፋኤልን በእለት ውሃ እየደገሙ ያጠምቋታል እንድትጠጣም ያደርጓታል። በቤት ውስጥ ጨሌ ይነሰነሳል፤ ምክንያቱም ቅድስት ድንግል ማርያም የሰውን ልመናና ተማጽኖ ሰምታ ትመጣለች ተብሎ ሰለሚታሰብ ነው። የጅብ ቆዳ ይነጠፋል፤ ጽንሱን ያፈጥናል ወይም ወደታች ያወርዳል ተብሎ ስለሚታመን ነው። ቅርንፉድ እና ቅቤ በማዋሀድ ወገቧ እና ሆዷ ይታሻል። ሆዷ በስሱ ልምድ ባላቸው እናቶች ሲታሽ ጽንሱ ቀስ በቀስ ወደታች ይወረዳል ተብሎ ስለሚታመን መሆኑ ይገለጻል (ተሳታፊ 04፤ ቃ.መ. 14/07/2015 ዓ.ም.)።

7. ጉልቻ የምጣድ የድስት መጣጃ ከሸክላ ወይም ከድንጋይ የሚዘጋጅ ሲሆን በቁጥርም ሦስት ናቸው፡፡ ሦስት ጉልቻ የትዳር ተምሳሌት ነው፤ሦስት ጉልቻ ይስጥህ/ሽ ይባላል፡፡ ሦስት ጉልቻ የአባት፣የእናትና የልጅን ጥምረት ያሳያል፡፡ አንዲት ነፍሰጡር ሴት ምጥ በሚጠናባት ጊዜ ትልልቅ እናቶች ትኩስ ጉልቻ በጆርባቸው በመያዝ ማርያም-ማርያም እያሉ ይማጸናሉ፡፡ ቅድስት ማርያም አንቺ የምጥን ነገር ታውቂዋለሽ ትዳሩ እንዳይበተን እመ ብርሀን (የብርሃን እናት) አንቺ ቅረቢያት፤አሳልፈሽ ለርኩሳን መናፍስት አታጋልጫት፤ባጠፋን ይቅር በይን፤ተለመኝን በማለት ይለማመናሉ፡፡ ሴቶቱ መቀነታቸውን ወንዶቹ ደግሞ ቀበቷቸውን ይፈታሉ፤ ድርጊቱ (የመሸነፍ፤ የመረታት፤ የይቅርታ ይደረግልን) ተማጽኖን እንደሚያመለክት መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ (ተሳታፊ 04፤ ቃ.መ. 14/07/2015 ዓ.ም.)

በአጋጣሚው ደም የመምታት ሁኔታው የከፋ ከሆነ የተለያዩ ተጨማሪ ክዋኔዎች ይካሄዳሉ። ከእነዚህም መካከል “ቱልት” የተባለ የእጽዋት ቅጠል ተቆርጦ በወገቧ ዙሪያ ላይ እንዲታሰር ይደረጋል (ደሙን ያቆማል ተብሎ ስለሚታመን ነው)፤ ብረት ምጣድ ይንኳኳል፣ ግርግዳ ይነደላል፣ ጥይት ይተኮሳል። እነዚህ ክዋኔዎች ከሰመመን ይመልሷታል ተብሎ ይታመናል። ክፉ መንፈስ የብረት ድምጽ አይወድም ተብሎ ይታመናል። ሰራቂ ወላዷ ደም ገብቶ ይይዛታል የሚል እምነት ስላለ እንደዚህ አይነት ክዋኔዎች የሚፈጸሙ መሆናቸውን መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ (ተሳታፊ 19፤ ቃ. መ 14/06/2015 ዓ.ም.)።

የተጠቀሱት ክዋኔዎች ተካሂደው ነፍሰጡሯ ከተገላገለች በኋላ፤ ነፍሰጡሯን ከእርኩስ መንፈስ የሚጠብቁ እና በጭንቅ ሰዓት ለነበረው ሰው ደስታ መግለጫዎች የእሷና የሕፃኑን/ኗን ጤና መጠበቂያ ክዋኔዎች ይካሄዳሉ። ይህን በተመለከተ መረጃ ሰጪዎች ሀሳባቸውን በሚከተለው መንገድ ያጋራሉ።

> ወዲያው እንደወለደች እልልታው ይቀልጣል፤ ለወንድ የደመቀ እልልታ ሰባት[8] ጊዜ የሚደረግ ሲሆን፤ለሴት ደግሞ በአንጻራዊነት የቀዘቀዘ እልልታ ይደረጋል። በባህሉ መሰረት የተወለደው/ችው ሴት ወይም ወንድ መሆኑ ወዲያው ስለማይነገር ሴትና ወንድ መሆኑ የሚታወቀው በዚሁ በእልልታው ወቅት በሚደረገው የጭብጨባ ሥርዓት ነው። ወዲያው የማርያም መሸኛ[9] ተብሎ ገንፎ ይገነፋል፤ጠላ ይበጠበጣል፤ ቢጠራም ባይጠራም ወዲያውኑ ይጠጣል፤ ቤተሰቡ አቅም ካለው የጾም ወቅት ካልሆነ ሊያርድም ይችላል፤ የቅርብ ጐረቤትም ገንፎው ጭብጦ የሚበላ የሚጠጣውን ወተት፤ የሚቀባ ቅቤ ይዞ ይመጣል፤ በሌላ በኩል አራሷን ርኩስ መንፈስ እንዳይቀርባት በማሰብ ድፍን ቅል፣ወንፊት አንካሴ ወይም ሌላ ብረት ነገር ከትራሷ ስር እንዲቀመጥ ይደረጋል። ከብረት የተሰሩ መሳሪያዎች በአጠገቧ እንዲቀመጡ የሚደረገው ርኩስ መንፈስ ብረት ባለበት አካባቢ አይጠጋም የሚል እምነት በማኅበረሰቡ አባላት ዘንድ ያለ በመሆኑ ነው። አራሷ እሳት ያልነከው ነገር እንዳትበላ ይከለከላል፤ ለዚህም ምክንያቱ ለሕጻኑ/ኗ ቁርጠት ይሆናል ተብሎ ስለሚታመን ነው። እስከ ሦስት ቀን ድረስ ከተገላገለችበት አካባቢ አትነሳም፤ አትታጠብም፤በሦስተኛው ቀን ግን ደም የነካው ልብስ በሙሉ በቅርብ ወዳጅ

8. *ሰባት ቁጥር ጥልቅ ምሳሌና ትርጓሜ አለው። በዕብራውያን ዘንድ ሰባት ቁጥር ፍጹም ቁጥር ነው። *. እግዚአብሔር ከሰኞ እስከ ዕሁድ ያሉትን ቀናት በሰባት ቁጥሮች ወስኗል። (መ-. ምሳሌ 24፥16)*. እስራኤላውያን ከግብፅ ባርነት ነጻ ወጥተው በሲና በረሃ ሲጓዙ ይመሩት የነበረው በሰባት ደመና ነበር። (ዘዳ 13፥21) *. እስራኤላውያን ኢያሪኮን ለሰባት ተከታታይ ቀናቶች እንዲዞሯት፣በሰባተኛው ቀን ደግሞ ሰባት ጊዜ እንዲዞሯት ታዘው ነበር። (ኢያሱ 6፥15) *. ጴጥሮስ ወንድሙን ይቅር እንዲለው የታዘዘው እስከ ሰባ ሰባት ጊዜ እንጂ ሰባት ጊዜ ብቻ አልነበረም። (ማቴዎስ 18፥21, 22) በመሆኑም ፈጣሪ አምላክ የምልዑ(የፍጹምነት) ተምሳሌት የሆነ ወንድ ልጅ ተገኘ (ወንድ ልጅ ደም ይመልሳል፣ባድማ ያስከብራል፣መከታና ጋሻ ይሆናል፣አደባባይ ያውላላ) በሚል እሳቤ የማብሰሪያ እልልታው ሰባት ጊዜ የሚጨበጨብ መሆኑን መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ (ተሳታፊ11፤ ቃ.ም.፤ 17/06/2015 ዓ.ም.)፡፡

9. ከተለያዩ የእህል አይነቶች ወላዷ በአራስነት ጊዜዋ እንድትመገብ ከተዘጋጀላት የገንፎ እህል ተወስዶ የማርያም መሸኛ ይዘጋጃል፡፡ ይህም የሚሆነው እመብርሃን ነፍሰጡሯን በሰላም አንዷን ሁለት ስላደረገቻት እሷን የማመስገንና የመሸኘት ሥርዓት መሆኑን መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ (ተሳታፊ20 ፤የቡድን ውይይት ፤21/09/2015 ዓ.ም.) ፡፡
10. ጥቁር ጤፍ የሚዘጋጅ በቅቤ እየተጨበጠ ለአራስ እናቶች መጠየቂያ የሚውል የምግብ አይነት ነው፡፡

> ወንዝ ተወስዶ ይታጠባል። እሷም ገላዋን ታጥባ የመኝታ ቦታ ትቀይራለች፤ ቅቤ ትቀባለች፤ከዚህ በኋላ ከብር የተሰራ ክታብ፣ድሪ፣ አልቦ ታደርጋለች። እነዚህ ሁሉ ክዋኔዎች የሚካሄዱት አራሷን ከክፉ መንፈስ ልክፍት ነጻ ለማድረግ በማሰብ ነው። የሕጻኑ/ኗ ልብስ ከእናቱ ልበስ ጋር አብሮ ይታጠባል፤ነገር ግን የሕጻን ልብስ ባጠቡት ሰዎች አናት ላይ እንዲሰጣ ይደረጋል፤ ምክንያቱም ልብሱ የትም ቢሰጣ አውሬ ቢተነፍስበት ሕጻኑ/ኗ ሊጎዱ ይችላሉ ተብሎ በመታመኑ መሆኑ ይገለጻል (ተሳታፊ 15፤ ቃ.መ.፣ 06/07/2015 ዓ.ም.)።

## 5.4 ድህረ ወሊድ ስርዓተ ክዋኔ

ይህ ጊዜ ነፍሰጡሯ ወልዳ ታጥባ ከተነሳችበት ጊዜ ጀምሮ የተወለደውን ልጅ ክርስትና እስከታስነሳ ያለውን የክዋኔ ሂደት ያካትታል። ከዚህ በኋላ ወላዷንና ሕጻኑን/ኗን የመንከባከብ ስራ ተጠናክሮ ይቀጥላል። በዚህ ጉደይ ላይ መረጃ ሰጪዎች በቡድን ውይይታቸው ወቅት ሀሳባቸውን እዲህ አጋርተዋል።

> ዘመድ ወዳጅ ለአራሷ ገንፎ፣ወተት፣ቅቤ፣ጭብጦ[10] እየያዘ በመምጣት ይጠይቃታል። ሀብት ያለው ቤተሰብ ከሆነ አባት ወይም አማት አንድ ጥገት አምጥቶ ሊሰጥ ይችላል። በዚህ ጊዜ አራሷ እንዳታደርጋቸው የሚከለከሉ ነገሮች አሉ፤ አራሷ እረክሳለች ተብሎ ስለሚታመን ጓዳ ገብታ ምግብ አታዘጋጅም። ከእሷ ጋር ሰው አብሮ አይበላም፤ የምግብ ትራፊዋም ለሰው አይሰጥም፤ ሕጻኑ/ኗ ከሰው አይን፣ከንፋስ እና ከሙብራት ይሸፈናል (ለአይኑ ጤንነት)፣በዚህ ወቅት ከሚከወኑ ክዋኔዎች አንዱ ግርዛት ነው። ግርዛት[11] የሚካሄደው በ8ኛዉ ቀን ሲሆን በዚህ ቀን በምጥ ጊዜ አብሮ የነበረ የቅርብ ዘመድና ጐረቤት ይጠራል፤ሁሉም ይሰበሰቡና ገንፎ ይገነፋል፤ ቅቤ ይታሻል፣ ጠላ ይበጠበጣል፤እናም በሀዘንና በጭንቅ የቆየው የወዳጅ ዘመድ መንፈስ እረፍት የሚያገኝበት ወላዷም ዘመድ ጐረቤቱን የምታመሰግንበት የመጀመሪያው ጊዜ ተደርጎ እንደሚቆጠር መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ (ተሳታፊ20፤የቡድን ውይይት፤21/09/2015 ዓ.ም.)።

ከዚህ በመቀጠል የሚከወነው ወላዷን ማጥመቅ ሥርዓት ነው። ሴት ልጅ ከወለደች በ20 ቀን፤ ወንድ ልጅ ከሆነ ደግሞ በ15 ቀን ጸበል ትረጫለች። ይህ ቀን ማለት እረክሳለች ከሚለው ሥርዓት መጠነኛ መንጻት የምታገኝበት ነው። ስለሆነም የሚያርሳት ቋሚ ሰው ከሌላት ለራሷና ለባለቤቷ

---

11. ዕብራውያን እግዚአብሔር ሕዝብ እንደመሆናቸውና ከሌሎች የዓለም ሕዝቦች እንዲለያቸው ብሎ ምልእክት ይሆነው ዘንድ ግርዛትን ሰጣቸው፡፡ እንግዲህ በግርዛት ሕዝቡ መሆናቸውን አሳወቃቸው፡፡ በመጽሐፈ ሌዋውያን ውስጥ በሙሴ በአገልጋዩ በኩል እንደተጻፈው “ሕፃን በስምንተኛው ቀን እንዲገረዝ ይሁን” (ዘሌዋዊያን 12፡3) ሲል አዘዛቸው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ “እግዚአብሔርን (ኤሎሂም ያህዌ) በፍጹም ልብህና በፍጹም ነፍስህ እንድትወደው፣ በሕይወትም እንድትኖር፣ አምላክህ እግዚአብሔር (ኤሎሂም ያህዌ) የአንተንና የዘርህን ልብ ይገርዛል” (ዘዳግም 30፡ 6) አላቸው፡፡ እንዲሁም “ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ በልቡና በሥጋው ያልተገረዘ ባዕድ በእስራኤላውያን መካከል የሚኖር ቢሆንም እንኳ ወደ መቅደሴ አይግባ” (ሕዝ. 44፣9) በማለት ለእዝቄል ይናገራል። በመሆኑም የእምነቱን ሥርዓት ተፈጻሚ ለማድረግ በሥጋው የግርዛት ሥርዓቱ የሚፈጸም መሆኑን መረጃ ሰጩዎች ይገልጻሉ (ተሳታፊ11፤ ቃ.ም.፤ 17/06/2015 ዓ.ም.)፡፡

የሚሆን ምግብ ልታዘጋጅ ትችለለች፤ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን ዘመድ ጐረቤት የቤቱን ሥራ ሃላፊነት ወስዶ በመከፋፈል አራሷን የማገዝ ተግባር ይካሄዳል። እንግዳ መቀበልና መሸኘት፤ ውሃ መቅዳት፤ለቤተሰብ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን የማሟላት ስራዎች ይካሄዳሉ። በድህረ ወሊድ የመጨረሻው ክዋኔ ክርስትና ማስነሳት ነው። ክዋኔው አራት ዓላማዎች አሉት። እነሱም፤- አንደኛ፡ ሕጻኑ/ኗ የእናት አባታቸውን ሃይማኖት የሚቀበሉበት በቤተክርስቲያን ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ የሚወለዱበት እናት አባት እምነት ሃይማኖታቸውን የሚያስተላልፉበት መንገድ ነው። ሁለተኛ፡ እናቲቱ የመንጻት ክዋኔ ፈጽማ በይፋ ከማኅበረሰቡ ጋር የምትቀላቀለበት፣ ቤተክርስቲያን መግባት የምትጀምርበት፤ በማነኛውም ማኅበራዊ ጉዳይ እንድተሳተፍ ግዴታ የሚጣልባት ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የምታደርግበት ነው። ሦስተኛ የመንጻት ክዋኔ ይካሄዳል፤ አንዲት ነፍሰጡር እንደወለደች ረክሳለች ተብሎ ስለሚታሰብ ለማንጻት ትጠመቃለች፤ አራተኛ ክርስትና መነሳት ነው፤ ከማኅበረሰቡ የምትቀላቀልበት ህጻኑ/ኗ እምነት ከተቀበለ በኋላ መሆኑን ለማየት ተችሏል። በዚህ እለት በሚቀርበው ምግብ በሚለበሰው አልባሳት ማኅበራዊ ደረጃ ይገለጽበታል። ክዋኔው የ"አጥር ወፍ አትስማሽ"ተብላ የተመረቀችው ምርቃት የደረሰ መሆኑ በደስታ የሚገለጥበት ሰዓት እንደሆነ መረጃ ሰሰጪዎች ይገልጻሉ(ተሳታፊ11፤ቃ.ም፤17/06/2015 ዓ.ም.)።

## 5.5 በ "አጥር ወፍ አትስማሽ" ስርዓተ ክዋኔ ሂደት ላይ የሃማኖታዊ እና የህገረሰባዊ እምነቶች ፋይዳ

### 5.5.1. ሃይማኖታዊ ክዋኔዎች እና እሳቤዎች

በክርስትና እምነት ነፍሰጡርነትን የሚጠብቅ እግዚአብሄር እንደሆነ ይታመናል። ለዚህም ነው በዙርያዋ ያሉ ሰዎች ነፈሰጡሯን "የአጥር ወፍ አትስማሽ" ብለው ከመረቁ በኋላ "በቸር ይመልስን"፣ "በቀኝ ያቁምሽ"፣ "ለማተብሽ ያብቃሽ" እና የመሳሰሉትን የመልካም ምኞት መገለጫዎች የሚናገሩት። ይህም በአንድምታ መረዳት እንደሚቻለው አንቺን በቀኝ አቁሞ፤እግዚአብሄር እኛንም በሰላም ጠብቆ፤በሰላም ያገናኘን በማለት ምኞታችውን የሚገልጽት። ቤተ ዘመድና የቅርብ ጎረቤቶች የነፍሰጡርነትና የአራስነት ጊዜዋን ጨርሳ ክርስትና ካስነሳች በኋላ እንኳን "ለማተብሽ አበቃሽ" እና "እንኳን ለዚህ አበቃሽ" በማለት ደስታውን እየገለጸ አምላኩን ያመሰግንበታል።

ከዚሁ የሃይማኖት እሳቤ ሳንወጣ ቅድስት ድንግል ማርያም በምጥ ጊዜ ታማልዳለች እንዲሁም አብራ ትቀመጣለች ተብሎ ስለሚታመን ከነፍሰጡርነት ጀምሮ "ማርያም ትቅረብሽ" በምጥ ጊዜ "ማርያም ታማልድሽ፣ የማርያም መቀመጫ ተብሎ "ጨፌ ይነሰነሳል"፤ ከወለደች በኋላ እንኳን "ማርያም ማረችሽ፣ ማርያም በሽልም ታውጣሽ፣ማርያም ታጫውትሽ" ይባላል። ሌላው ከሃይማኖት እሳቤ ጋር የተያያዘው ጸበል እስከምትረጭ ድረስ እረክሳለች ተብሎ ይታመናል። ይህ ማለት ጓዳዋ ገብታ መገልገል አትችልም። ዕቃዎችን ብትነካ ዕቃው ሁሉ ይረከሳል ተብሎ ይታመናል። በዚህ ወቅት አራሷ የቤት ውስጥ መገልገያዎችን አትነካም። እንደወለደች ገንፎ ይገነፋል እና የማርያም መሸኛ ተብሉ ይበላል፤ በጥቅሉ ሲታይ በምጥ ጊዜ ቅድስት ድንግል ማርያም ታዳሚና አዳኝ ናት የሚል እሳቤ በማኅበረሰቡ ውስጥ እንዳለ ይገለጻል (ተሳታፊ03፤ ቃ.መ.፤ 12/09/2015 ዓ.ም.)።

### 5.5.2. ሀገረሰባዊ እምነቶች እና እሳቤያቸው

በዚህ ስር ማኅበረሰቡ በሕይወት ልምዱ ያገኛቸው ከእምነት ጋር ግንኙነት ያላቸው (Religious folklore) ሀሳቦች በስፋት ያንጸባርቃሉ፤ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ክዋኔዎችንም ይፈጸማሉ። ከእነዚህ መካከል፡- ነፍሰጡርን ነፍሰጡር ናት ብሎ በይፋ መናገር እሷን እና ጽንሱን ለክፉ አዳጋ ያጋልጣል ብሎ ማመን፤ነፍሰጡርነቷን በግልጽ አለመጥራት። በዚህ ምክንያት በተለያዩ ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ፈቃድ እንኳ ለመጠየቅ እሷ ደካማ ናት ተብሎ መናገር፤ሌላው ቀርቶ እሷን በጣም ትክ ብሎ ማየት አግባብ አለመሆኑ፤ ነፍሰጡር ሴት የምታየውን የመሰለ ሰው ትወልዳለች ተብሎ እምነት ማሳደር፣ በመሆኑም መልከ ጥፉ ሰው አይይሽ፣ መልከ መልካሙ ሰው ይመልከትሽ የሚሉ ማኅበረሰባዊ አባባሎችና አስተሳሰቦች ጎልተው የሚንጸባረቁበት መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

ሀገረሰባዊ እምነት በምጥ ጊዜ የበለጠ የሚከዎንበት አጋጣሚ አለ፣ ምክንያቱም በምጥ ጊዜ የጭንቅ ነገር ካጋጠመ ነፈሰጡሯን እና ሕጻኑን/ኗን ከክፉ መንፈስ ይታደጋል ተብሎ የሚታሰበው ነገር ሁሉ ይፈጸማል። መረጃ ሰጪዎች በቡድን ውይይት ወቅት "አንድ ወላድ ከተገላገለች በኋላ ከመጥፎ መንፈስ እንድትጠበቅ ብረት ከአልጋ እንጨት ጋር አብሮ ይታሰራል፣ድፍን ቅል ከአልጋው አናት ይደረጋል፣ የደም ግፊት ሲመታት ብረት ምጣድ ይኳኳል፣ ጥይት ይተኮሳል" በማለት ገልጸዋል (ተሳታፊ13፣የቡድን ውይይት፣ 21/08/2015ዓ.ም. ዓ/ም)። ከገለጻው መረዳት እንደሚቻላው ነፍሰጡርነት እና ምጥ ለወላዷም ሆነ ለቤተሰብና ለጐረቤት የጭንቅና የስጋት ወቅት በመሆኑ ለነፍሰጡሯ እና ለሕጻኑ/ኗ በማኅበረሰቡ የደህንነት መጠበቂያ መንገዶች ናቸው ተብለው ስለሚታሰቡ ከላይ የተዘረዘሩት የተለያዩ ሀገረሰባዊ እምነቶች የእነደሚከናወኑ መረዳት ይቻላል።

### 5.5.3 ከነፍሰጡርነት እና ከውልደትጋር የተያያዘ አባባሎች

በዚህ ስር ለነፍሰጡሯ እና ለሕጻኑ/ኗ ደህንነት፣ለመልካም ምኞት እና ፍላጎት መግለጫ የሚሆኑ አባባሎች (ብሂሎች) ይነገራሉ።

#### 5.5.3.1 ከወሊድ በፊት የሚነገሩ አባባሎች

አባባሎች የነፍሰጡር ሴቶች የመልካም ምኞት መግለጫ ስልቶች ስለሆኑ ማኅበረሰቡ ሀሳቡን ለመግለጽ ይጠቀምባቸዋል።

**የአጥር ወፍ አትስማሽ**፡- ይህ አባባል ነፍሰጡርነት ከታወቀ ጀምሮ ሰዎች ለነፍሰጡሯ ባላቸው ማሰብና መጨነቅ ምክንያት ሰላምታ በተለዋወጡ ቁጥር፣ ከቤት ጉዳይ ኑሮ ገብቶ የበላ፣ የጠጣ፣ ሰው በሙሉ የምረቃት ማሳረጊያው "የአጥር ወፍ አትስማሽ"፣ ምጥሽ ሳይጸና በሰላም በጤና ተገላገይ ማለት ነው።

**ማርያም ትቅረብሽ**፡- አንዲት ነፍሰጡር በሰላም እንድትገላገል ከመመኘት የተነሳ በክርስትና እምነት ደግሞ ቅድስት ድንግል ማርያም በምልጃ ጊዜ ታማልዳለች ተብሎ ስለሚታመን ሁሉም ሰው ጸሎት እና ምኞቱን ለመግለጽ ሲባል የሚነገር ነው።

**ማርያም በቀኝ ታቁምሽ፡-** የእርግዝና ጊዜ የጭንቀትና የስጋት ወቅት ስለሆነ በግራ በመወከል በቀኝ ያቁምሽ በማለት ይመረቃሉ፣ ማለትም ከግራ ወደ ቀኝ (የተሻለ ጊዜ) ያደርስሽ፣በሰላም ተገላገይ ለማለት ነው።

**የሆድሽን በጀርባሽ ያርግልሽ፡-** ነፍሰጡሯ ያረገዘችው ጽንስ በሰላም ለቋት አንዷ ሁለት ሁና ልጅሽን ለአንቀልባ ያብቃልሽ የሚል ይዘት ያለው የመልካም ምኞት መግለጫ ነው።

**በእርጥብ ቅጠል ያስቀምጥሽ፡-** ይህ አባባል ምጥ ሲጀምር ጫቅማ ቅጠል፣በኩበት ላይ ተነጥፎ እንድትቀመጥ ይደረጋል። በሰላም ለመገላገያ ቀንሽ ያድርስሽ ለማለት ነው። ከመውለጃ ቀን በፊት ውርጃ ወይም ሌላ ህመም አይምጣብሽ እንደማለት ነው። ከላይ እንደምናየው በአንድ በኩል መልካም ምኞችን ይገልጹበታል። በሚያምነው እምነት ይማጸንላታል። በዚህ መሰረት ማርያም ትቅረብሽ እና ማርያም በቀኝ ታቁምሽ በማለት ሀሳቦች ላይ በቅድስት ድንግል ማርያም መለመኑ ማኅበረሰቡ ለእምነቱ ያለውን ጽናት ማሳያ ነው። በእናቶች አስተሳሰብ ቅድስት ድንግል ማርያም ልጅ ወልዳለች ምጥን እና ነፍሰጡርነትን ታውቃለች፣ ስለዚህ ይህንን ጭንቅ እናቶች ሲገጥማቸው የእሷን ስም ሲጠሩ በመንፈስ ትቀርባቸዋለች ተብሎ ስለሚታመን ቅርብ አድርገው በማመን ማርያም በቀኝ ታቁምሽ፣ ማርያም ትቅረብሽ ብለው ለነፍሰጡሯ መልካም ምኞት እንደሚገልጹላት መረጃ ሰጪዎች ያብራራሉ (ተሳታፊ18፣ ቃ.ም.፣ 12/05/2015 ዓ.ም.)።

### 5.5.3.2 በወሊድ ጊዜ እና ከወሊድ ጊዜ በኋላ የሚባሉ አባባሎች

**ማርያም በሽልም ታውጣሽ፡-** ነፍሰ ጡሯ ከተገላገለች በኋላ ቅድስት ድንግል ማርያም በሰላም እንድትገላገይ እንዳደረገችሽ አሁንም ጠብቃ ከልላ ጤናሽ እና ውበትሽ ሳይጓደል የአራስነት ጊዜ ተጠናቆ ከማኅበረሰቡ ጋር ተቀላቀይ ለማለት የሚነገር የምኞት መግለጫ ነው።

**ማርያም ታጫውትሽ** ፡-ይህ የሚባለው ነፍሰጡሯ ከተገላገለች በኋላ ሲሆን፣ በዚህ በአራስቤት ቆይታዋ መጥፎ መንፈስ ይተናኮላታል ተብሎ ስለሚታመን ቅድስት ድንግል ማርያም አብራሽ ትሁን ወይም አትለይሽ መጥፎ መንፈስ አይቅረብሽ ማለትን ያመለክታል።

**ለማተብሽ ያብቃሽ፡-** ይህ አባባል በክርስትና እምነት መሰረት አንድ ወላድ ማለትም ጸበል እስክትረጭ ድረስ እረክሳለች ተብሎ ይታመናል፣ ከእሷ ጋር ሌላ ሰው አይበላም ይህንን ቀን አልፋ ልጇን አስጠምቃ በሰላም ክርስትና አስነስታ እንድትጨርስ ያላቸውን ምኞት ለመግለጽ የሚናገሩት ብሂል ነው።

**እንኳን ማርያም ማረችሽ፡-** በክርስና እምነት ቅድስት ድንግል ማርያም ምጥ የተያዘች ሴት ስትማጸን ትመጣለች፣ ታማልዳለች፣ ተብሎ ይታመናል። ለዚያም ጉልቻ ተሸክመው ቅድስት ድንግል ማርያምን ይለምናሉ። የቅድስት ድንግል ማርያም ማረፊያ የሚሉት ስትገላገልም ቀድመው ገንፎ አገንፍተው የማርያም መሸኛ ያደርጋሉ።

**እንኳን ለማተብሽ አበቃሽ /እንኳን ለዚህ አበቃሽ** ፡-እነዚህ አባባሎች የሚነገሩት ከማኅበረሰቡ መቀላቀለ ለበቃች እናት ነው። እንኳን ለዚህ አበቃሽ የሚለው በውስጡ አምላክን ማመስገን ነው።

ከዚያ የነፍሰጡርነት የስጋትና የሀሳብ ጊዜ እንዲሁም የምጥ ሰዓት ወጥተሽ ለዚህ አደረሰሽ፣ በሙሉ ጤንነትሽ ልጅሽን አዝለሽ ወደ ትክክለኛው ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ አበቃሽ ለማለት ነው።

በሌላ በኩል እንኳን ለማተብሽ አበቃሽ ማለት ከክርስትና በኋላ የሚባል ሲሆን፣ አራሷ ከ15 እስከ 20 ቀን ድረስ ከምግብ በመጠቀሚያ ዕቃ ሁሉ ተለይታ ትቆያለች። ክርስና እስከታስነሳ ድረስ ቤተክርስቲያን አትገባም፣ከሌሎች ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ትገደባለች፣ ስለሆነም እንኳን ወደ ቀድሞ ሁኔታሽ ተመለስሽ የሚል አገላለጽን የያዘ ነው።

**ለአራስ ትሰጡት ብታጡ ውሃ በቅል አምጡ፡**- ይህ ብሂል ሁለም ሰው አራስን አቅሙ የፈቀደውን ይዞ መጠየቅ እንዳለበት የሚገልጽ የማኅበረሰብ የሞራል ልዕልና ማሳያ ነው።

**አራስ የእጇን ትልስ**፡- በማኅበረሰቡ እሴት መሰረት አራስን መንከባከብ የሞራል ግዴታ ነው። ለአራስ ሴት የማይራራ እና የማያዝን የለም። ቤት ያፈራውን እጅ የሰጠውን የማይሰነዝር የለም። በተለየ ሁኔታ ደግሞ እሷም ለአራስ እናቶች ታደርገው የነበረው እንክብካቤና ድጋፍ የሚገለጸው በዚህ ሰዓት መሆኑን የሚያሳይ አባባል ነው።

**እመጫት ሆደ ቅርጫት፡**- ይህ አባባል ዋና ዓላማው ወልደው የሚያጠቡ እናቶች ምግብ በደንብ መመገብ ያለባቸው መሆኑን በሌላ በኩል ደግሞ የማኅበረሰቡ አባላትም ይህን ተረድተው ለአራሷ ቤተ ያፈራውን በመያዝ መጠየቅ እንደሚገባቸው ማሳያ መሆኑን መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ (ተሳታፊ01፣የቡድን ውይይት፣26/09/2015 ዓ.ም.)።

### 5.5.4 "የአጥር ወፍ አትስማሽ" ማኅበረ ባህላዊ ፋይዳው

በጥናቱ ተተኳሪ የማኅበረሰብ አባላት መካከል የመረዳዳትና የመተጋገዝ ባህል ከሚገለጽባቸው የተለያዩ ሥርዓተ ከበራዎች መካከል አንዱ "የአጥር ወፍ አትስማሽ" ሥርዓተ ክዋኔ ነው። አንዲት ነፍሰጡር ሴት ብቸኝነት እንዳይሰማት ከእርግዝና ጋር በተያያዘ ከሚመጣ ድባቴ (depression) ውስጥ እንዳትገባ እንዲሁም የኢኮኖሚ ችግር ካለበት ጭንቀት(stress) ውስጥ ሆና እሷንም ሆነ ሕጻኑን/ኗን እንዳትጎዳ ጎረቤት ወዳጅ ዘመድ በምክር፣ በገንዘብ፣ ድጋፍ ያደርጋል። "...ነፍሰጡር ሴትን ማገዝ፣ በአራስነት ጊዜዋ የምትመገባቸውን ምግቦች ቀድሞ በጋራ ማዘጋጀት ትልልቅ እናቶች ባሳለፋቸው የእርግዝና ጊዚያት ያጋጠሟቸውን ተሞክሮዎች እያነሱ የሚያጋሩበት መልካም አጋጣሚ እንደሆነ መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ (ተሳታፊ03፣የቡድን ውይይት፣25/09/2015 ዓ.ም.)።

ነፍሰጡር ሴቶች በሚወልዱበት ጊዜ እናቶች ወደ አራሷ ቤት በመሄድ የሚያደርጉት የማበረታታት፣ የመጠየቅና በሀሳብ የመደገፍ እንግዳ የማስተናገድ ሥርዓት በመካከላቸው ያለውን ማኅበራዊ ትስስር የበለጠ ለማጠናከር ያገለግላል። ለወላዷ የማኅበረሰቡ አባላት ቤት ያፈራውን፣አቅም የፈቀደውን በመያዝ የሚያደርጉት የመጠየቅ ባህል በወሊድ ጊዜ አራሷ የፈሰሳትን ደም ለመተካት ወገቧ ጠንክሮ ጉልበቷ ተመልሶ ወደ ቀደመ አቅሟ በቶሎ እንድትመለስ የሚጫወተው ሚና የላቀ ነው። ይህም በማኅበረሰቡ አባላት መካከል የሚደረገውን የመረዳዳትና የመተጋገዝ ልማድ በባህሉ እሴት ውስጥ በመትከል ዘላቂነቱን ለማረጋገጥ ያግዛል። "...የአጥር ወፍ አትስማሽ ሥርዓተ ክዋኔ ማኅበረሰቡ በሥራ፣በሀሳብና በገንዘብ የሚያደርገው የመተባበርና የመደጋገፍ ሥርዓት በአባላቱ

መካከል ያለውን ትስስር ከማጠናከሩም በላይ ዘለቄታውን በማረጋገጥ ረገድ የላቀ ሚና የሚጫወት መሆኑን" መረጃ ሰጪዎች ከሕይወት ልምዳቸው በመነሳት ያብራራሉ (ተሳታፊ09፣ቃ.ም፣ 23/09/2015 ዓ.ም.)።

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ "በአጥር ወፍ አትስማሽ" ሥርዓተ ክዋኔ አማካኝነት የጥናቱ ተተኳሪ የማኅበረሰብ አባላት አዎንታዊ ጉዳዮችን በመትከልና በማስቀጠል፣ከባህሉ የሚያፈነግጡ እኩይ ድርጊቶችን ደግሞ በመቆጣጠርና የማኅበረሰቡን በጎ እሴቶች በማስቀጠል ከባህሉ ጋር ለሚዛመዱ ጠቃሚ ዘመናዊ አስተሳሰቦች መዳበርና መጎልበት አስተዋጽዋቸው የላቀ መሆኑን ያሳያል።

## 6. ማጠቃለያ እና ምክረ ሐሳብ

### 6.1. ማጠቃለያ

በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ "የአጥር ወፍ አትስማሽ" ሥርዓተ ክዋኔና ፋይዳ በጃቢ ጠህናን ወረዳ ምን እንደሚመስል የመረጃ ትንተና የተካሄደበት ሲሆን፣የአጥር ወፍ አትስማሽ ምንነትን፣ የአጥር ወፍ አትስማሽ ስርዓተ ክዋኔና ፋይዳ ከእርግዝና እስከ ክርስትና ማስነሳት ድረስ ያለውን ስርዓት እንዲሁም ከክዋኔው ጋር ያሉ ሃይማኖታዊና እምነታዊ እሳቤዎች ምን እንደሚመስሉ ታይቷል፣፣ በተጨማሪም በክዋኔ ውስጥ ያሉ አባባሎች ይዘትንም ለማብራራት ተሞክሯል። በመሆኑም ከጥናቱ የሚከተሉት ግኝቶች ተለይተዋል።

- የ "አጥር ወፍ አትስማሽ "ስርዓተ ክዋኔ ቁሳዊ ባህልን፣ስነ ቃልን፣ ሀገረሰባዊ እምነቶችን እና ልማዶችን አካቶ የያዘ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፣

- ከጥናቱ መገንዘብ እንደሚቻላው የ "አጥር ወፍ አትስማሽ ሥርዓተ ክዋኔ" በጥናቱ ተተኳሪ ሁሉም ቦታዎች ላይ ተመሳሳይ በሆነ መንገድ የሚከወን አለመሆኑ ተለይቷል፣፣

- ለ "አጥር ወፍ አትስማሽ" ሥርዓተ ክዋኔ መነሻ ሃይማኖታዊ አስተምሮ እና ሀገረሰባዊ እምነቶች ሆነው ይታያሉ። ምክንያቱም በአንድ ክዋኔ ላይ ሁለቱም ተግባራዊ ሲደረጉ ይታያል፣ ለምሳሌ ምጧ የጠናባት እናት እንድትገላገል ከፊሉ ጉልቻ ይዞ ቅድስት ድንግል ማርያምን ይማጸናል፣ቀሪው ደግሞ የጅብ ቆዳ ያነጥፋል፣ ሌሎችም ክዋኔዎች ከዚሁ ጋር የተመሳሰሉ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፣

- በጥናቱ ለማየት እንደተቻለው ብዙዎች ክዋኔዎች ከክርስትን እምነት ጋር የተየያዘ መነሻ ያላቸው መሆናቸውን ለማየት ተችሏል፣ለዚህም ማሳያው በነፍሰጡርነት "ማርያም ትቅረብሽ"፣ ስትወልድ "የማርያም መሸኛ"፣"እንኳን ማርያም ማረችሽ"፣ "ማርያም በሸልም ታውጣሽ" የሚሉ የመልካም ምኞት መግለጫ አባባሎች እንዳሉ ታይቷል፣

- የ"አጥር ወፍ አትስማሽ" ሥርዓተ ክዋኔ አንድ የሕይወት ዑደት ሁኖ በውስጡ ግን አራት የተለያዩ ሁነቶችን እንዳሉት ታይቷል፣አነሱም፣- አንደኛ ነፍሰጡርነት ተደጋግሞ የሚመጣ ዑደት ቢሆንም በተከሰተ ጊዜ ሁሉ በልዩ እይታ ይታያል፣ ሁለት ውልደት /ዘርን መተካት

/ይህ አንድ የሕይወት ዑደት ተደርጎ ይወሰዳል። ሶስተኛ የመንጻት ክዋኔ ይካሄዳል፣አንዲት ነፍሰጡር እንደወለደች ረክሳለች ተብሎ ስለሚታሰብ ለማንጻት ትጠመቃለች፣፡ አራተኛ ክርስትና መሰነሳት ነው፣፡ እናቲት ከማኅበረሰቡ የምትቀላቀልበት ሕጻኑ/ኗ እምነት ከተቀበለ በኋላ መሆኑ ተለይቷል።

- የ "አጥር ወፍ አትስማሽ" ሥርዓተ ክዋኔ የእናትና ሕጻንን ጤና ለማስጠበቅ ብሎም የዘር ግንድን ለማስቀጠል እንዲሁም ማኅበረሰቡ እርስ በእርስ ተግባብቶና ተዋዶ ማኅበራዊ አንድነቱን ለማስጠበቅ ፋይዳው የጎላ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፣

- በ "አጥር ወፍ አትስማሽ" ስርዓተ ክዋኔ ሂደት ላይ የማይሳተፍ የማኅበረሰብ ክፍል የለም፣ ሽማግሌዎች ይመርቃሉ፣ ካህናት ያጠምቃሉ፣ ክርስትና ያነሳሉ ሴቶች በሙሉ ስራ ያግዛሉ፣የሚበላ የሚጠጣ ይዘው ይጠይቃሉ፣ ወንዶች ባህሉ በሚፈቅደው ዐውድ ላይ በመገኘት የድርሻቸውን እንደሚወጡ ጥናቱ አሳይቷል፣

- ማኅበረሰቡ ለሕጻናትና ለእናቶች ልዩ እንክብካቤና አመጋገብ እንደሚያስፈልጋቸው በሀገረሰባዊ እውቀቱ ተገንዝቧል፣ ለዚህም ነው ነፍሰጡር አማረኝ ያለችውን ሁሉ ማሟላት ግዴታ የሚሆነው፣፡ እንዲሁም ወልዳ የተኛችን አራስ የተሻለ ትመገብ ዘንድ አቅም በፈቀደ መጠን ወተት፣ሥጋ፣ገንፎ፣ጭብጦ፣የመሳሰሉትን በመያዝ መጠየቅ የሞራል ግዴታ መሆኑን ለመለየት ተችሏል፣

- በ "አጥር ወፍ አትስማሽ" የክዋኔ ሂደት ሃይማኖት እና ሀገረሳባዊ እምነቶች ተዋህደው አንዲት ነፍሰጡር ሴት ከእርግዝናዋ ቀን ጀምሮ ወልዳ ክርስትና አስነስታ ከማኅበረሰቡ ጋር መቀላቀል እስከምትችል በተለያየ ሁነትና ዐውድ ውስጥ በርካታ ሥርዓተ ክዋኔዎች የሚካሄዱ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል።

### 6.2. ምክረ ሐሳብ

- የ "አጥር ወፍ አትስማሽ" ሥርዓተ ክዋኔ ሂደት በአንዲት ሴት ላይ እርግዝና ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ ወልዳ ክርስትና አስነስታ ወደ መደበኛ ማኅበራዊ ተሳትፎ እስከምትቀላቀል ድረስ የማኅበረሰቡ አባላት አቅም በፈቀደ መጠን ለወላዷ ድጋፍና እንክብካቤ ስለሚያደረጉላት፣ በሂደቱ እናቲቱን ከጭንቀትና ከድባቴ ከኢኮኖሚያዊ ችግር እንድትወጣ የሚያግዝ በመሆኑ ለወጣት ነፍሰጡር ሴቶቸ እናቶች ተሞክሯቸውን የሚያጋሩበት መንገድ እንዲፈጥሩ የሴቶችና ሕጻናት ባለሙያዎች እገዛና ድጋፍ ቢያደርጉላቸው፣

- የ"አጥር ወፍ አትስማሽ" ስርዓተ ክዋኔ ማኅበራዊ ፋይዳው ከፍ ያለ በመሆኑ ማኅበረሰቡ እንደነዚህ አይነት የማኅበረሰብን ትስስር የሚያጠነክሩ እሴቶች እንዲጎለብቱ ባህል ቱሪዝም በጥናት ላይ የተመሰረተ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ቢፈጥር፣
- በ"አጥር ወፍ አትስማሽ" ስርዓተ ክዋኔ የሚደረጉ ባህላዊ የሥነ ልቦና ድጋፍና እንክብካቤዎች ለነፍሰጡር ሴቶች ያለው ፋይዳ የላቀ በመሆኑ የበለጠ ውጤታማ

የሚሆኑበት መንገድ በጥናት ላይ ተመስርቶ ዳብሮና ጎልብቶ ተግባራዊ የሚሆንበት መንገድ የባህል ቱሪዝም ባለሙያዎች ቢፈጥሩ፣

- የ"አጥር ወፍ አትስማሽ" ክዋኔያዊ ሥርዓት(ወፊቱ አትስማሽ) እና በተለያ ስያሜዎች እንደሚጠራ፣ በእስልማና እምነት ተከታዮች ዘንድም "ፋጢማ ቆሪማ" እየተባለ ክዋኔያዊ ስርዓቱ እንደሚካሄድ ለማስተዋል ተችሏል፣ ክዋኔያዊ ስርዓቱ ለነፍሰጡሯ ሥነ ልቦናዊ እና አካላዊ ደህንነትን፣ ለሕጻኑ/ኗ ምቾትን ሊያጐናፅፍ የሚችል ማኅበረሰባዊ እሴት በመሆኑ ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ ባህል ቱሪዝም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ሃላፊነቱን ቢወጣ፣
- የ "አጥር ወፍ አትስማሽ" ክዋኔያዊ ሂደቱና ትውፊቱ የሚገኘው በቃል ግጥሞች አማካኝነት በመሆኑ፣በጊዜ ሂደት ማኅበራዊ እሴቱ ሊደበዝዝና ሊጠፋ ስለሚችል በጽሑፍ መልክ ተሰንዶ እንዲቀመጥ ቢደረግ የተሸለ ይሆናል።

## ዋቢ ጽሑፎች


ሱባባ አህመድ። (2012 ዓ.ም.)። "በኢሉ አባቦር ዞን በዶረኒ ወረዳ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረግ ሥርዓት ትንተና" ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ኤም.ኤ. ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት። ጅማ ዩኒቨርስቲ፣ያልታተመ።

መሐመድ አሊ። (2012 ዓ.ም.)። "ፋይዲ ባህላዊ ጋብቻ እና የሰርግ ስነ-ስርዓት በአፋር በራህሌ ወረዳ ማህበረሰብ" ለፎክሎር ኤም.ኤ. ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት። ባህርዳር ዩኒቨርስቲ፣ ያልታተመ።

ሙሉቀን የኔሰው። (2011ዓ.ም.)። "የለውጥ ሽግግር በባሶሉበን ማህበረሰብ ባህሊዊ የሠርግ ሥርዓት" ለፎክሎር ኤም.ኤ. ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት። ባህርዳር ዩኒቨርስቲ፣ያልታተመ።

ስራዬ እንዳለው። (2005 ዓ. ም)። "የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓተ ክዋኔዎች በፍኖተሰላም አካባቢ" ለፎክሎር ኤም.ኤ. ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ያልታተመ።

ሽታየ ገዕኖሬ። (2011 ዓ.ም.)። "የከምባታ ብሄረሰብ ባህላዊ ጋብቻ የቋንቋ አጠቃቀም ትንተና" ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ኤም.ኤ. ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት። ጅማ ዩኒቨርስቲ፣ያልታተመ።

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ። (1948 ዓ.ም.)። *መጻፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክስ ማተሚያ ቤት።

አፀደ ተፈራ። (2007 ዓ.ም.)። "የዋግኽምራየወሊድ፣ የጋብቻ እና የሞት ስነ-ስርዓት ፋይዳ ትንተና" በፎክሎር መርሃ ግብር የዶክትሬት ድግሪ ከፊል ማሟያ ጥናት። አድስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ያልታተመ።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር። (1962)። *መጽሐፍ ቅዱስ፣ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት*። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል። (1993)። *አማርኛ መዝገበ ቃላት*። አዲስ አበባ።

እንድሪስ አወል። (2012 ዓ.ም.)። "የሕይወት ሽግግር ሥርዓት ርዕዮተ ዓለማዊ ትንተና በቤንች ብሔረሰብ" ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ኤም.ኤ. ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት። ጅማ ዩኒቨርስቲ፣ ያልታተመ።

ያለው እንዳወቀ። (2004 ዓ.ም.)። "የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር"። አድስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ፈቃደ አዘዘ። (1991 ዓ.ም.)። የስነቃል መምሪያ። አዲስ አበባ፣ አርቲስት ማተሚያ ቤት።

Canda, Edward. R. (1988). *Therapeutic Transformation in Ritual, Therapy, and Human Development.* Journal of Religion and Health, Vol. 27, No. 3 pp. 205-220, Published by: Springer

Dundes, A. (1980). Interpreting Folklore India. Indiana፡ University Press.

Dorson, M. R. (1972). Folklore and Folk Life: An Introduction. Chicago: The University of Chicago press

Gennep, A. van. (1960). *The Rites of Passage* (M.B. Vizedom & G.L. Caffee, Trans.). London: Routledge & Kegan Paul.

Gladys Ifeoma (2019) Significance and Use of Cultural Symbols in the Contemporary African Society: IGBO Symbols as a Paradigm Mgbakoigba, Department of Igbo, African and Asian Studies Nnamdi Azikiwe University, Awka Journal of African Studies.Vol 8, No. 1 gladudechukwu@gmail.com Research Practices Published by Routledge, New Fetter Lane,

Rappaport, Roy A. (1992) Folklore, Cultural Performances, and Popular Inc Hatboro, Pennsylvania; Republished by Gale Research Company, Book Tower, Detroit.

Rudnicki, S., Graham, J., Habboushe, D., & Ross, R. (2001). Social support and avoidant coping: Correlates of depressed mood during pregnancy in minority women. Women & Health.

Sims, Marth, and Marthine Stephens (2005). Living Folklore: An Introduction of The Study of People and Their Tradition, State University Press.

Turner, Victor. (1967). *The forest of symbols*. United States of America Cornell University Press.